የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ህዳር ፳ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 7
ADDIS ABABA, 29th November, 2018


<u>ማውጫ</u>


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፰/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ለተወዳሪነት እና ስራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………………………… ገጽ ፲ሺ፮፻፴፪


**<u>CONTENT</u>**


Proclamation No.1098/2018

International Development Association for Financing Competitiveness and Job Creation Project Ratification Proclamation ..........................................................Page 10632


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፰/፪ሺ፲፩

### <u>መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የተጨማሪ የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

ለተወዳሪነት እና ስራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፩፻፳፩ ሚሊዮን ፯፻ ሺ ኤስዲ አር (አንድ መቶ ሀያ አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ) ኤስ ዲ አር የሚያስገኘው ተጨማሪ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እኤአ ጁን ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓም ባካሄደው ስብሰባ

## PROCLAMATION No. 1098/2018

### <u>A PROCLAMATION TO RATIAFY THE ADDITIONAL LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERANATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION</u>

**WHEREAS,** the Additional Loan Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the the Government of the Federal Republic of Ethiopia a loan amount of one hundred twenty one million seven hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 121,700,000) for financing competitiveness and job creation Project ,was signed in Addis Ababa on the 29th day of June 2018;

**WHEREAS,** the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on

ያፀደቀው በመሆኑ፤

]

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታወጇል፡፡

፩. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ አዋጅ "ለተወዳሪነት እና ስራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የተጨማሪ የብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፰/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>**የስምምነቱ መፅደቅ**</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ ጁን ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 6263-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫.<u>**የገንዘብ ሚኒስቴር ስልጣን**</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፳፩ ሚሊዮን ፯፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ ሀያ አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ) ኤስ ዲ አር በብድር ስምምነቱ በተገኙት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬.<u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በነጋት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፳ ቀን ፪ሺ፲፩**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

the 6th day of November , 2018 ;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. <u>**Short Title**</u>

This Proclamation may be cited as ‘’ International Development Association for Financing Competitiveness and Job Creation Project Ratification Proclamation No.1098/2018’’

2. <u>**Ratification of the Agreement**</u>

The Loan Agreement Number 6263-ET signed in Addis Ababa on the 29th day of June 2018 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

3. <u>**Power of the Ministry Finance**</u>

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary of the utilization of the Loan amount of equivalent to one hundred twenty one thousand Special Drawing Rights (SDR 121,700,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 29th day of November, 2018**

**SAHIL WORK ZEWUDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**